# የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የህዝብ ቤተመጽሀፍት
# የዲሲ የህዝብ ቤተ-መፃህፍት ፖሊሲ፣ በታዎችን እና ፕሮግራሞችን ለመሰየም እና ለለጋሾች እውቅና ለመስጠት

## ዓላማ

የዚህ ፖሊሲ አላማ የዲሲ የህዝብ ቤተ መፃህፍትን (ቤተ-መፃህፍት) በታዎችን እና ፕሮግራሞችን የመሰየም እና የስም-ቅያሬ የማድረግ ስልጣን እና ሂደትን ማቋቋም ነው። ይህ ፖሊሲ በጎረቤት ቤተመጻሕፍት እና በማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር መታሰቢያ ቤተመጻሕፍት የውስጥ እና የውጪ በታዎችን እንዲሁም የዋና ዋና ፕሮግራሞች ስያሜን ያካትታል።

ከዚህ ፖሊሲ ጋር በሚስማማ መልኩ፣ የለጋሾች የገንዘብ መዋጮ ልዩ እውቅና  መስጠት በለጋሽ ግድግዳ ላይ በማስቀመጥ እና/ወይም በልገሳ የተደገፉ የግብይት እና የፕሮግራም ቁሳቁሶች ላይ እውቅና በመስጠት ብቻ ይከናወናል። የለጋሾች አስተዋፅዖ በቤተ መፃህፍት በታዎች ላይ ስያሜ በመስጠት እውቅና አይሰጠውም።

ይህ መመሪያ የዲሲ የህዝብ ቤተ መፃህፍት ህንፃዎችን ስያሜ አይመለከትም። የዲሲ የህዝብ ቤተ መፃህፍት ህንፃዎች የስም አሰጣጥ ፖሊሲ በ19 DCMR§ 808 ውስጥ ይገኛል።

## የውስጥ/የውጭ በታዎችን እና ዋና ፕሮግራሞችን የመሰየም ስልጣን

ለማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር የመታሰቢያ ቤተ መፃህፍት ወይም የአካባቢ ቤተ መፃህፍት ውስጣዊ እና ውጫዊ በታዎች የቀረቡ ሁሉም የመታሰቢያ ስያሜ ሀሳቦች በቤተ-መፃህፍቱ ባለአደራዎች ቦርድ ይፀድቃሉ፡፡። ለፕሮግራሞች የመታሰቢያ ስያሜ ሀሳቦች በቤተ-መፃህፍቱ ዋና ዳይሬክተር ይፀድቃሉ።

የቤተ-መፃህፍቱ ባለአደራዎች ቦርድ ማንኛውንም የቦታ ስያሜ ሀሳቦችን ውድቅ የማድረግ መብት አለው። ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬከተሩ ማንኛውንም የፕሮግራሞች ስያሜ ሀሳቦችን ውድቅ የማድረግ መብት አለው።

## በታዎችን እና ፕሮግራሞችን ለመሰየም የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

የቤተ-መፃህፍቱ ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር እና/ወይም ተወካይ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለመሰየም እድሎች የምርጫ ሂደትን ይመሰርታሉ። የተሰየሙ በታዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፣ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይወሰኑም፥ የጥናት ክፍሎች፣ የመሰብሰቢያ ክፍሎች፣ የዝግጅት በታዎች፣ አዳራሾች፣ የፕሮግራም ክፍሎች እና የአትክልት በታዎች።

በቤተ-መጽሐፍት ውስጥ ያሉ የውስጥ/ውጫዊ በታዎች ከሚከተሉት መመዘኛዎች አንዱን ወይም ከዚያ በላይ በሚያሟሉ ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች ወይም ተልዕኮ-ጋር በተያያዙ አካላት ስም ሊሰየሙ ይችላሉ፥

- ለቤተ-መጻህፍቱ ያልተለመደ አገልግሎት የሰጡ ወይም በሌላ መንገድ ልዩ የሆነ እውቅና የሚሰጣቸው፤
- ለኮሎምቢያ ዲስትሪክት ትልቅ አስተዋፅዖ ያደረጉ፤
- የዲስትሪክቱ ነዋሪ ሆነው እያሉ ጉልህ ስኬት ያስመዘገቡ፤
- ለቤተ-መጻሕፍት፣ ለንባብ ወይም ለሥነ ጽሑፍ ዓለም ትልቅ አስተዋጽዖ ያደረጉ።

እንዲህ ያለ ስያሜ ለቤተ-መጻሕፍቱ ያለውን አጠቃላይ ጥቅም በጥንቃቄ ለማጤን የእያንዳንዱን የስም አሰጣጥ ሀሳብ ተገቢው ግምገማ ይደረጋል። እንዲህ ያለ ተገቢ የግምገማ እርምጃ የሚከተሉትን ያካትታል፥

- ስያሜው በቤተ-መፃህፍት ላይ አዎንታዊ ማሳያ እንደሚሆን እና ሆኖ እንደሚቀጥል የመወሰን ግምገማ፤
- ከቤተ-መጻህፍት ባለአደራዎች ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶችን ጨምሮ በቤተ መፃህፍቱ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ማንኛውም ሊከሰቱ የሚችሉ የፍላጎት ግጭቶችን መገምገም፤
- በቤተ-መፃህፍቱ ላይ ሊያንጸባርቁ የሚችሉ ሌሎች ማንኛውም ሁኔታዎች።

የመታሰቢያ ምልክት ማድረጊያ ወጥ የንድፍ መመዘኛዎች ይከተላሉ፣ የንጣፎች እና ሌሎች ምልክቶች በታ በቤተ-መፃህፍቱ ዋና ዳይሬክተር የሚወሰኑ ናቸው።

የቤተ-መፃህፍቱ ዋና ዳይሬክተር ወይም ተወካይ ለቦታዎች እና ፕሮግራሞች ስም አሰጣጥ ሂደትን ያዘጋጃል፣ የመመዘኛ ደረጃዎች ያወጣል፣ እና መመሪያዎችን ያዘጋጃል።

## የሕዝብ ግብዓት

የቤተ-መፃህፍት ቦታዎች እና ፕሮግራሞች መሰየም የህዝብ አስተያየት እና ግምገማ ያስፈልገዋል። ቤተ-መፃህፍቱ የህዝብን አስተያየት ለመሰብሰብ፣ ለምሳሌ የዳሰሳ ጥናቶች፣ የመስመር ላይ ግብረመልስ እና በቤተ-መፃህፍት ባለአደራዎች ቦርድ ስብሰባዎች ላይ የህዝብ አስተያየትን ለመሰብሰብ ግልፅ ሂደትን ያዘጋጃል።

ህብረተሰቡ አስተያየት ለመስጠት እድል እንዲያገኘው የስያሜ ሀሳብ/እቅድ ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል። የቤተ-መፃህፍት ቦርድ በስም አሰጣጥ ሀሳብ ላይ ድምጽ ከመስጠቱ በፊት የህዝብ ግብአት ውጤቶች በቤተ-መፃህፍት ድረ-ገጽ ላይ ይለቀቃሉ።

## የስሞች ቆይታ እና የስም ለውጦች

ግለሰብ ወይም ግለሰቦችን፣ ቤተሰብን ወይም ከተልዕኮ-ጋር-የሚያያዝን አካል ለማክበር የመሰየም መብቶች በአጠቃላይ ለውስጣዊ/ውጫዊ ቦታ ወይም ፕሮግራም ጠቃሚ ህይወት የሚቆዩ ናቸው ተብሎ ይጠበቃል፣ በሌላ መንገድ ካልተገለጸ በስተቀር።

በቤተ-መፃህፍት ውስጥ የተሰየመ ቦታ በከፍተኛ ሁኔታ ከታደሰ (ከአዲስ ሕንፃ ጋር የሚመጣጠን አዲስ ጠቃሚ ሕይወትን በመስጠት)፣ ወይም በቤተ-መጽሐፍት ላይ ጉልህ የሆነ ተጨማሪ ነገር ካለ፣ ቦታው እንደገና ሊሰየም ይችላል። እንደዚህ ባሉ አጋጣሚዎች፣ ዋናው ስም በሌላ ቦታ ላይ በሥራ አስፈፃሚው ዳይሬክተር ጥቆማ እና በቤተ-መፃህፍት ባለአደራዎች ቦርድ ይሁንታ፣ ወይም በስራ አስፈፃሚው ዳይሬክተር ውሳኔ ፕሮግራም ሊከበር ይችላል።

ይህ ፖሊሲ በፀደቀበት ጊዜ ያሉ የውስጥ/የውጭ ቦታዎች ስሞች ወይም የስጦታ እውቅናዎች ተፈጻሚነት ሆነው ይቀጥላሉ።

## የስም መወገድ

ለስም እውቅና መስጠት የታማኝነት እና የሲቪክ አመራር ባህሪያትን ለሚያሳዩ ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች እና አካላት ይሰጣል። የስም አሰጣጥ ቁርጠኝነት የተደረገለት ግለሰብ፣ ቤተሰብ ወይም አካል እነዚህን መስፈርቶች በማንኛውም ጊዜ የሚጥስ ከሆነ፣ ቤተ-መፃህፍቱ የግለሰቡን፣ የቤተሰቡን ወይም የህጋዊ አካሉን ስም ከስያሜው እድል ለማስወገድ ሊመርጥ ይችላል።

በቤተ-መፃህፍቱ የባለአደራዎች ቦርድ የፀደቀ ማንኛውም ስያሜ መሻር የሚቻለው በዚያው አካል ድምጽ መስጠት ብቻ ነው። የቤተ-መፃህፍት ባለአደራዎች ቦርድ የአንድን ፕሮግራም ስም የመሰረዝ ስልጣንን ለስራ አስፈፃሚው ዳይሬክተር ውክልና ይሰጣል።